# የጸሎተ ሐሙስ ሥርዐተ ሕፅበት

ከስቅለት ዐርብ በፊት የሚውለው ሐሙስ በክርስቲያኖች ዓለም በተለያየ ስም ይጠራል ። ለምሳሌ ሀ ጸሎተ ሐሙስ ይባላል ፡- ይህም መድ፡ኃኒታ ችን ክርስቶስ ሐዲስ ሥርዐተ ቁርባንን በሠራበት ጊዜ የጸለየውን ጸሎት ያስ ታውሳል ። ይህ ብቻ አይደለም ፡ ከሥ ርዐተ ቁርባን በኋላ ሊገድሉት በሚፈ ልጉት ሰዎች እጅ ከመያዙ በፊት በጌቴ



ክርስቶስ ስለ ክፉ አድራጊዎች በጌቴ ሴማኒ ጸለየ



www.ethiopianorthodox.org

ሴማኒ ውስጥ የጸለየውንም ጸሎት ያመለክታል ፤ በጌቴሴማኒ የጸለየው ሐሙስ ለዐርብ አጥቢያ ነውና ።

ለ የነፃነት ሐሙስ (ሺ.ርተርስዴይ ) በመባል ይጠራል። ይህ ስያሜ ክርስቶስስ በዕለተ ሐሙስ ሥርዐተ ቁርባንን በሰየመበት ወቅት ሥጋው በመስቀል ላይ ስለ ኃጢአት ይቅርታ እንደሚቆረስ ደሙም በመስቀል ላይ ስለ ብዙኃን ደኅንነት እንደሚፈስ የተናገረውን ቃል ያመለክታል ። ከዚህም ሌላ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ ከኃጢአት ባርነት ነፃነት እንደሚያገኙ የሚያመለክተው የፋሲካ በግ ተሠውቶ ክርስቶስና ደቀ መዝሙርቱ የነፃነትን በዐል ለመጨረሻ ጊዜ በአንድነት አክብረዋልና በዚህ ምክንያት የነፃነት ሐሙስ ተብሎ አል ።



ክርስቶስ በጸሎተ ሐሙስ ማታ ሥርዐተ ቊርባንን ለደቀ መዛሙርቱ አሳየ ።

ሐ ሞንዲ ሐሙስ ይባላል ፤ ይህም ትእዛዘ ሐሙስ ማለት እንደሆነ በቃሉ የሚጠቀሙ ክርስቲያኖች ይናገራሉ ፤ በዕለተ ሐሙስ ሐዲስ ትእዛዝና ሐዲስ ሥርዐት መስጠቱን ያሳስባል ። ሐዲስ ሥርዓትና ሐዲስ ትእዛዝ የምንለው ፡- ሥርዐተ ኦሪት ተለውጦ ሥርዐተ ወንጌል መተካቱን ፤ በትእዛዘ ኦሪት ምትክ ትእዛዘ ወንጌል መታወጁን ለመግለጥ ነው ። ይህም ሁሉ የሆነ በጸሎተ ሐሙስ ዕለት ነው ። በተጨማሪም ሞንዲ የሚለው ቃል በእንግሊዝኛ (ሞኒ) ገንዘብ የሚለውን ቃል ስለሚጠጋ የስጦታ ቀን ማለት እንደሆነ የሚተረጉሙት አሉ ። ከዚህም የተነሣ የምዕራብ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በጸሎተ ሐሙስ ዕለት ገንዘብ አበባና ሌላም ልዩ ልዩ ስጦታ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይወስዳሉ። ይህ ተግባር ክርስቶስ ኅብስቱን አንሥቶ “ይህ ሥጋዬ ነው እንኩ ብሉ ፤ ይህ ደሜ ነው እንኩ ጠጡ” በማለት በጸሎተ ሐሙስ የፈጸመውን ድርጊት በግልጥ ያሳያል ።

መ ፔድላቪዩም ፡- ሕፅበተ ሐሙስ ማለት ነው ይህ ደግሞ መድኃኒታችን ክርስቶስ ከእራት በኋላ የደቀ መዛሙርቱን እግሮች ማጠቡን ለማስታወስ የተሰጠ ስያሜ ነው ። ክርስቶስ በዚህ ዓለም በኖረበት ጊዜ የፈጸማቸው ድርጊቶች ሁሉ በቤተ ክርስቲያን በተለያየ መልክ ሲታወሱ ይኖራሉ ። በተለይ በዚህ ጽሑፋችን በጸሎተ ሐሙስ ዕለት የተፈጸመው ሥርዐተ ሕፅበት በዓለም ባለች ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት ትርጓሜና መታሰቢያ እንዳለው እንገልጣለን ።

1ኛ/ አብዛኛዎች የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በጸሎተ ሐሙስ ዕለት ሊቀ ካህናቱ ወይም ጳጳሱ በቤተ ክርስቲ



www.ethiopianorthodox.org

ያን የተገኙ የምእመናንን እግር በውኃና በወይን ቅጠል ያጥባል በኢትዮጵያ ኦ. ተ.ቤ. ክርስቲያንም ከዚህ ያልተለየ ሥርዐት ይፈጸማል ።

2ኛ በላቲን ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሱ (ፓፓው) የዐሥራ ሁለት ክርስቲ

ይህ ሥርዐት በቀጥታ ፊደል በፊደል ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን እግር እንደ አጠበ ለማሳየት ያህል ነው ።

3ኛ/ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ በዚሁ በጸሎተ ሐሙስ ዕለት ሊቀ ካህናቱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ

ዲሁም ሊታጠቡ የሚችሉ አልባሳትን ሁሉ ያጥባል ። በግልጥ አነጋገር ቤተ ክርስቲያኑን ያጸዳል ። ስለዚህም ጸሎተ ሐሙስን እንደ ዝግጅት ቀን ይቆጥሩ ታል ። የትንሣኤን በዐል በደመቀ ሥነ ሥርዐት ለማክበር ከዚያ በፊት ሐሙስ



ጌታችን ኢየሱስ ከእራት በኋላ የደቀ መዛሙርቱን እግር በማጠብ ትሕትናን አስተማረ

ያኖችን እግሮች ብቻ ያጥባል ከማጠ ቡም በፊት ከዮሐንስ ወንጌል ምዕ ራፍ ዐሥራ ሦስት 1 - 20 ያነብባል ።

ያሉትን ንዋያተ ቅዱሳት ያጥባል ፤ ለምሳሌ ፦ መሠውያውን ፤ ዕዋዎችን የቤተክርስቲያኑን ወለልና ግድግዳ እን

ሁሉን ነገር ያጸዳሉ በአጠቃላይ አስ ሳሰብ ፦ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርተ እግሮች ማጠቡ ቤተ ክርስቲያንን ከ



www.ethiopianorthodox.org

ጢአት እንደ አነጻት ማመልከቱ ነው ብለው ይተረጉማሉ ። ይህ አይነት ሥርዓት በተለይ በአስጳንያ (ስፔይን) ቤተ ክርስቲያን እስካሁን ይታያል ። የተጀመረውም በ588 ዓ.ም. ነበር ። በዐሥረኛው ምእት ዓመት ደግሞ በሮም ቤተ ክርስቲያን ተለመደ ።

4ኛ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ሥርዐተ ሕፅበትን በተለየ በተራ ምሳሌ ያሳያሉ ። ይኸውም ካህኑ የእራት ግብዣ ያዘጋጃል ፤ የተጋባዦችን እጅ ያስታጥባል የምግብ ማቅረቢያ ዕቃዎችንም ሁሉ ያጥባል ይወለውላልም ። እንግዲህ ይህ ሁሉ አስተሳሰብ ክርስቶስ በትሕትና ለፈጸመው ድርጊት በተጨባጭ ሁኔታ መታሰቢያ ለማድረግ መሆኑን ማንም ክርስቲያን ይረዳዋል ። ግን ለመታሰቢያነቱ የሚስማማ ትክክለኛው ሲምቦል (አምሳል) የትኛው ነው? ቢባል ይህ ልክ ነው ፤ ያኛው ልክ አይደለም ማለት የሚቻል አይመስልም።

ምክንያቱም ሁሉም የክርስተቶስን ትሕትና አምነው መታሰቢያውን በልዩ ልዩ መልክ ለመግለጥ ሞክረዋልና ።

በጸሎተ ሐሙስ ከእራት በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን

እግር ለምን አጠበ ?

1ኛ ይህን ተግባር ደቀመዛሙርት ራሳቸው ማድረግ ሲገባቸው አላደረጉምና በእነርሱ ፋንታ የእነርሱን ሥራ ለመሥራት ነው ። 2ኛ መልካም ምሳሌ ለመሆን ነው ፤ መምህርና ጌታ ሲሆን ይህን ታላቅ ትሕትና መፈጸሙ ለደቀ መዛሙርቱ ዐቢይ ትምህርት ይሆናቸዋልና ። 3ኛ ክርስቶስ በዚያ ዘመን የነበረው ኅብረተሰብ የሚያደርገውን



የክርስቶስን አርአያ በመከተል የኦርቶዶክስ ቤ ክርስቲያን መሪ እግር ሲያጥብ



www.ethiopianorthodox.org

መልካም ልማድ ሁሉ ያደርግ ነበር ። ለምሳሌ ፡- በጥንቱ በአይሁድ ኅብረተሰብ ዘንድ እንግዳን መቀበልና መጋበዝ ፤ ከግብዣውም በኋላ ወይም በፊት የእንግዳውን እግሮች ማጠብ በጣም የተለመደ ነበር ፤ ያው ግን ደግነትና ትሕትና ሆኖ ይቆጠር እንደ ነበር ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል ። ስለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች ማንበብ በላይ የገለጥነውን ሀሳብ ለማስተዋል እንደሚረዳ እንገምታለን (ዘፍጥ 18 ፤ 4 ፤ 24 ፤ 32 ፤ መሳፍ 19 ፡ 21 ፤ 1 ጢሞ 5. 10) ።

በመጨረሻ ይህን ጽሑፍ እንዲህ እናጠቃልላለን ፡ ክርስቶስ እንደሠራ መሥራት አንችልም ። ሆኖም የሠራውን ሁሉ ለእኛ በሚረዳን መንገድ መግለጥ እንችላለን የሠራውን መታሰቢያ ሁሉ ለትውልደ ትውልድ ማቆየት ለክርስቲያኖች ተቀዳሚ ተግባር መሆኑን የቀደሙን አስተማሩን።እኛም ለሚከተሉት እናስተምራለን።ዛሬ የእንግዶችን እግሮች ተንበርክኮ ለማጠብ ጊዜው አይፈቅድ ይሆናል፤ምክንያቱምእግርን ብቻ ሳይሆን አካልን በሙሉ ለመታጠብ የሚያስችል መታጠቢያ ቤት ተዘጋጅቶአልና ። ስለዚህ ክርስቶስ እግር በማጠብ የፈጸመውን ምግባረ ትሕትና በማናቸውም መልካም ሥራ መግለጥ እንደሚቻል እንማራለን ለሌሎችም እናስተምራለን ።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

www.ethiopianorthodox.org